
ቅዱስ አቡነ ኪሮስ
@sealideaconge

መልክዐ አቡነ ኪሮስ-ግዕዝ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ አሜን። ንቄጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ጽሒፈ መልክዐቲሁ ለብፁዕ ወለቅዱስ ገዳማዊ አቡነ ኪሮስ ጸልዮቱ ወበረከቱ የሀሎ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን።

፩. ዕፁብ ገድልከ ወመንክርከ ጎያል፤ እምነ አድባራት ዘኤሊ ስሙዓነ ዜና ወገድል፤ ጻድቅ ኪሮስ ተወካፌ ኪዳን ወቃል፤ ለዘተአመነ በጸሎትከ ኢትዮጵያዊ ባዕል፤ እስመ አድኃንከ እመንሱት ወኃጕል።

፪. ሰላም ለዝክረ ስምከ ጎበ ዐምደ ወርቅ ዘተጽሕፈ፤ ምስለ ስመ አበው ጌራን እንተ ትከውን ውክፈ፤ ጻድቅ ኪሮስ እንተ ታገኒ አእላፈ፤ አባ ሀበኒ ለወልድከ ሰማያዊተ ምዕራፈ፤ ወዘመላእክት አስኬማ ወዐፅፈ።

፫. ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ ወለርእስከ በእማኔ፤ ወለገጽከ ጽዱል እንተ ተሳተፈ ሥነ ሱራኔ፤ ጻድቅ ኪሮስ ምዑዘ ምግባር እምርኔ፤ እምግብረ ሰይጣን ዘኢለመደ ርኅራኄ፤ ናሁ እሴፎ ኪያከ ባላሄ።

፬. ሰላም ለቀራንብቲከ ወለአዕይንቲከ ፍሱሓት፤ ለአእዛኒከ ሰላም ተወካፍያተ ስሱ ቃላት፤ ጻድቅ ኪሮስ ዘኢትስዓር በሞት ሞትከሰ ውዕቱ ፍልሰት፤ መንገለ ሕዕኖሙ ለአበው ቀደምት።

፭. ሰላም ለመላትሒከ እምጽጌረዳ ቀይሀ፤ ወለአእናፊከ ሰልም ዘምስለ ፍናፍር ፍሡሕ፤ ጻድቅ ኪሮስ ኮከበ ገዳም ብሩህ፤

የአቡነ ኪሮስ መልክዕ በአማርኛ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን። ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ የገዳማዊ የብፁዕ ወቅዱስ አባታችን የአቡነ ኪሮስን መልክዕ መጻፍና ማንበብ እንጀምራለን። ጸሎታቸው በረከታቸው ከሕዝበ ክርስቲያኑ ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን።

1. ዕፁብ ገድልከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! በዜና እና በገድል ዝናቸው ከተሰማ አድባራትን ከዞሩ ቅዱሳን ይልቅ ገድልህ ዕፁብ ነው፤ ተአምርህም ገናና ነው፤ ቃል ኪዳን የተቀበልህ አቡነ ኪሮስ ሆይ! በጸሎትህ የታመነ ኢትዮጵያዊ ባለ ጸጋን ከጥፋትና ከፈተና አድነኸዋልና።

2. ለዝክረ ስምከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ከደጋግ አባቶች ስም ጋር አንድ ሆኖ በዐምደ ወርቅ ላይ ለተጻፈው የስም አጠራርህ ሰላምታ ይገባል፤ ብዙዎችን ለፈጣሪ የምታስገዛ ጻድቁ ኪሮስ አባቴ ለልጅህ ሰማያዊት ቤትን አዘጋጅልኝ፤ የመላእክትን አስኬማና መጐናጸፊያም ስጠኝ።

3. ለሥዕርተ ርእስከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለራስህ ጠጕር ሰላምታ ይገባል፤ ለራስህም እጅ በመንሳት ሰላምታ ይገባል፤ የብርሃንን ደም ግባት ለተመላ ለሚያበራ ፊትህም ምስጋና ይገባል፤ ከሽቱ ይልቅ ምግባርህ የሚጣፍጥ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! ርኅራኄን ከማያውቅ ከሰይጣን ሥራ እነሆ አንተን አማላጁን እማፀናለሁ።

4. ለቀራንብቲከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል፤ ለሚያበሩ ዐይኖችህም ሰላምታ ይገባል፤ ከፈጣሪ ስድስቱ ቃል ኪዳናትን ለተቀበሉ ጆሮዎችህም ሰላምታ ይገባል፤ በሞት የማትለወጥ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! ሞትህማ ወደ ቀደመ አባቶች ዕቅፍ መሸጋገር ነው።

5. ለመላትሒከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ከጽጌረዳ ይልቅ ቀያይ ለሆኑ ጕንጮችህ ሰላምታ ይገባል፤ ከሚያስደስቱ ከንፈሮች ጋር ለአፍንጫዎችህም ሰላምታ ይገባል፤ የምታበራ የገዳም ኮከብ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! ለደጋጐች

ሀበኒ እምዋማከ ዋማ ቅድስና ወንጽሕ፣ አመ ለኄራን ይከውን ወይገብእ ፍትሕ፣

፤

፩. ሰላም ለአፉከ ዘሰዐሞ ክርስቶስ፣ ወለአስናኒከ ሰላም ምህዳራተ ልሳን ቅዱስ፣ ጻድቅ ኪሮስ ኮከበ ኤልያስ፣ ሜላተ ጺጋከ ወዘዚኣከ መንፈስ፣ ይሰወጥ ላዕሌየ በሥጋ ወነፍስ፡፡

፪. ሰላም ለቃልከ አበሳ ብዙኀን ደምሳሲ፣ ወለእስትንፋስከ ሰላም ቍሱላነ ሥጋ ፈዋሲ፣ ጻድቅ ኪሮስ ለዘሰአልኩከ ብእሲ፣ ማኅደረ ዚኣየ ማኅደረ ዚኣከ ረሲ፣ እስመ በዓለ ቤት አንተ ወአነ ፈላሲ፡፡

፫. ሰላም ለጕርዔከ ወዘዚኣከ ክሣድ፣ ለመትከፍትከ ሰላም በመልዕልተ ዘባን ውዱድ፣ ጻድቅ ኪሮስ ዘመንፈስ ቅዱስ ማኅፈድ፣ ያስተበፅዑከ ሰማያውያን ነገድ፣ እለ ይገሥሡ እሳተ በእድ፡፡

፬. ሰላም ለእንግድዓከ ወለሕፅንከ በኢሌልዮ፣ ለአእዳዊከ ሰላም ስፉሐት ለጸልዮ፣ ጻድቅ ኪሮስ ቀስታመ መስቀል ዘቀራንዮ፣ አባ ሀበኒ ለወልድከ ዘኢይትኀፈር ርእዮ፣ እስመ ጸላዒ ላዕሌየ አብዝኀ እከዮ፡፡

፭. ሰላም ለመዛርዒከ አክናፈ መንፈስ ዘተመሰላ፣ ወለኵርናዕከ ሰላም ምስለ እመትከ በላዕላ ጻድቅ ኪሮስ ለማርም እምታኅተ ሥዕላ፣ ሶበ ሰገድከ ደነኒከ ስግደታ ኵላ፣ የአክል እንዘ ትብል ሰማዕከ እምቃላ፡፡

፲፩. ሰላም ለእራኅከ ወአጻብዒከ ዐሠርቱ፣ እለ ያበርሁ ዘልፈ ምስለ አጽፋፈ እድ እሙንቱ፣ ቅዱስ ኪሮስ ሡቱፈ ቅዱሳን ተስዓቱ፣ አርፍቀኒ ውስተ ሕፅንከ ጊዜ

ቅዱሳን ፍርድ ፈጽሞ በተደረገ ጊዜ ከበረከትህ የቅድስና እና የንጽሕና ዋጋን ስጠኝ፡፡

6. ለአፉከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ክርስቶስ ለሳመው አፍህ ሰላምታ ይገባል፣ ለከበረ አንደበትህ ማደሪያ ለሆኑ ጥርሶችህም ሰላምታ ይገባል፣ እንደ ኤልያስ የገዳም ኮከብ የሆንህ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! መጐናጸፊያህና በአንተ ላይ ያደረ መንፈስ ቅዱስ በሥጋም ሆነ በነፍስ በእኔ ላይ ይደር፡፡

7. ለቃልከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! የብዙዎችን በደል ለሚያስተሰርይ ቃልህ ሰላምታ ይገባል፣ በሥጋና በነፍስ ቍስለኞችን ለሚፈውስ እስትንፋስህም ሰላምታ ይገባል፣ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! አንተ ባለቤት እኔ ስደተኛ ነኝና ለተማፀንሁህ ለእኔ የአንተን ቤት የእኔ ቤት አድርግልኝ፡፡

8. ለጕርዔከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለጕሮሮህ እና ለአንገትህ ሰላምታ ይገባል፣ በጀርባ ላይ ለተስማማ ትከሻህም ሰላምታ ይገባል፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆንህ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! በእጅ እሳትን የሚዳስሱ ሰማያውያን መላእከት ያመሰግኑሃል፡፡

9. ለእንግድዓከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ባለመለየት ለደረትህና ለእቅፍህ ሰላምታ ይገባል፣ ለጸሎት ለተዘረጉ እጆችህም ሰላምታ ይገባል፣ አባቴ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! ለእኔ ለልጅህ ሳየው የማላፍርበትና ድል የምነሳበትን የቀራንዮ መስቀል ስጠኝ፡፡

10. ለመዛርዒከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! የመንፈስ ቅዱስ ኀይልን ለተመሉ ጡንቻዎችህ ሰላምታ ይገባል፣ በላይ ከክንድህ ጋር ለአለች ክርንህም ሰላምታ ይገባል፣ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ሥዕል በታች ዘጠኝ እልፍ ስግደታቱን ኹሉ በሰገድህ ጊዜ ‹ወዳጄ ኪሮስ ይበቃሃል› ስትል ከሥዕሏ ቃልን ሰማህ፡፡

11. ለእራኅከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለመኻል እጅህ ሰላምታ ይገባል፣ ከእጅህ ጥፍሮች ጋር ለሚያበሩ ለእኒህ ለዐሥሩ ጣቶችህም ሰላምታ ይገባል፣ ከተስዓቱ ቅዱሳን ጋር በክብር አንድ የሆንህ ቅዱስ አባ ኪሮስ ሆይ! ከዚኸ ዓለም በሞት በተወሰድሁ ጊዜ ልቤ ዕረፍትን ሲሻ በእቅፍህ ላይ አሳርፈኝ፡፡

ልብየ ይፈቱ፤ አመ ፍልሰትየ ለዓለም ዝንቱ።።

፲፪. ሰላም ለገቦከ በሐሩረ ፀሐይ ዘተመንደበ፤ ወለከርሥከ ሰላም በእብነ ብልቲት ዘሰከበ፤ ጻድቅ ኪሮስ ረስየኒ መዝገበ፤ ወአልብወኒ መንፈሳዊተ ጥበበ፤ ረስየኒ ወልደ ረሰይኩከ አበ።።

፲፫. ሰላም ለኵልያቲከ ወለኀሊናከ ዘጠንቀቀ፤ ምሕረተ ነዳያን ሕዝብ ወለአማዑቲከ ጥዩቀ፤ ጻድቅ ኪሮስ ዘትሜሕር ጽድቅ፤ አንሥአኒ በየማንከ ዓቅመ ኀሊናየ ጽኑቀ፤ እስመ ዘከማከ ኄር ያነሥእ ዘወድቀ።።

፲፬. ሰላም ለንዋየ ውስጥከ ማዕከለ ከርሥ ሰፍኒ፤ ወለኀንብርትከ ሰላም ጣዕመ ማሕሌት መናኒ፤ ጻድቅ ኪሮስ ሠቱፈ መቃርዮስ ወእንጦኒ፤ ቅናተ ትኅትና ወጽድቅ ከመ ያቅንተኒ።።

፲፭. ሰላም ለአቍያጺከ ወለአብራክከ ዘይትዋሐዳ፤ ምስለ አጻብዕ ወአእጋር ለእግዚአ ስብሐት ሶበ ይሰግዳ፤ ጻድቅ ኪሮስ ትሩፈ ምግባር ዘእምሲኖዳ፤ ምግባረ ዚኣከ አመዕለተ ጽኑዕ ፍዳ ይሠልጥ ወይፍዲ ዘዚኣየ እዳ።።

፲፮. ሰላም ለሰኳንዊከ ለምሕሮ ወንጌል ዘይደክማ፤ ወለመከየድከ ሰላም እንበለ ተሐውኮ ዘቆማ፤ ጸዋሬ መስቀል ኪሮስ ወለመላእክት አስኬማ፤ በንዋየ ሐቅሉ ኢይሰብዐኒ መስቴማ አስተርእዮ ሊተ ዘዚኣከ ግርማ።።

12. ለገቦከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! በፀሐይ ሐሩር ለተሠቃየ ጐንህ ሰላምታ ይገባል፤ በሚያቃጥል ባልጩት ድንጋይ ላይ ለተኛ ሆድህም ሰላምታ ይገባል፤ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! እኔን ባሪያህን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አድርገኝ፤ መንፈሳዊት ጥበብንም ግለጽልኝ፤ አባቴ አድርጌሃለሁና ልጅህ አድርገኝ።።

13. ለኵላያቲከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለኵላሊትህ ምስጋና ይገባል፤ ለተቸገሩ ሕዝቦች ምሕረትን ለሚያስብ ኀሊናህም ሰላምታ ይገባል፤ እውነትን የምታስተምር ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! ኀሊናዬ በፈለገው መጠን በቀኝ እጅህ አንሣኝ።።

14. ለንዋየ ውስጥከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! በሆድ መካከል ላለ ለተትረፈረፈ ንዋየ ውስጥህ ሰላምታ ይገባል፤ የምግብን ጣዕም ለናቀ ለእምብርትህም ሰላምታ ይገባል፤ ከአባ መቃርዮስና ከአባ እንጦንዮስ ጋር በክብር አንድ የሆንህ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! መንፈሳዊ ትጥቅን ታስታጥቀኝ ዘንድ ኀይልህ ለእኔ ኀይል ይሁነኝ።።

15. ለአቍያጺከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለጭኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ ለእግዚአብሔር ሲሰግዱ ከጣትና ከእግር ጋር አንድ ለሆኑ ጒልበቶችህም ሰላምታ ይገባል፤ እንደ አባ ሲኖዳ ምግባር ትሩፋትህ የበዛ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! የአንተ ሥራ (ምግባር) በጽኑ ፍርድ ቀን አበሳ ዕዳዬን ፈጽሞ ይክፈልልኝ።።

16. ለሰኳንዊከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ወንጌልን ሲያስተምሩ ለአልደከሙና ለአልታከቱ ተረከዞችህ ሰላምታ ይገባል፤ ያለመናወጥ ጸንተው ለቆሙ መሐል እግሮችህም ሰላምታ ይገባል፤ መስቀልንና የመላእክትን አስኬማ የተሸከምህ ጻድቅ አባ ኪሮስ ሆይ! ሰይጣን በጦሩ ድል እንዳያደርገኝ ድል አድራጊ ግርማህን አሳየው።።

፲፮. ሰላም ለአጻብዒከ ወለአጽፋረ እግርከ ኵሉ፤ ለቆምከ ሰላም ለአዳም መልክዐ ሥዕሉ፤ ጻድቅ ኪሮስ ለዐቢይ በከመ ባሕሉ፤ በዓለመ ሥጋ አመ ዓለመ ነፍስ አዐሉ፤ ሰአል ሊተ ምሕረተ እምላዕሉ፡፡

፲፯. ሰላም ለመልክዕከ ዘኅብረ ሥነ ተነክረ፤ ጸአተ ነፍስከ እምበድነ ሥጋከ ጊዜ ልበ አምላክ ሠምረ፤ ምሕረተ ኃጥኣን ኪሮስ ዘበልብከ ኃደረ፤ እምቦ ዘጸልዓ ኪያከ ኄረ ሕይወቶ ዘጸልዓ ወሞተ አብደረ፡፡

፲፱. ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ በመዐዛ ከርቤ ወሜዓ፤ ወለመቃብሪከ ሰላም በሥምረተ ክርስቶስ ንጉሥ መርዓ፤ ጻድቅ ኪሮስ አመ ይደምጽ ቀርነ ውውዓ፤ ያኅቱ ማኅቶትከ ዘዚኣየ ቅብዐ፤ አርአያ አብዳን ኪከዊንየ ኢይቆም በአፍአ፡፡

፳. ሰላም ለኪሮስ ዘሰአመ ነደ በከናፍር፤ ወጸለሎ በደመና እግዚአብሔር፤ ከመ ትፃእ ነፍሱ ዘእንበለ ጻዕር፤ ዳዊት ኃለየ ወይቤ በመሰንቆ ሐዋዘ መዝሙር፤ ለጻድቅ ብፁዕ ሞቱ ክቡር፡፡

፳፩. አምኀ ሰላም ኅዳጠ ለከ አቅረብኩ፤ እስመ እምንእስየ አበ ኪያከ ረሰይኩ፤ ጻድቅ ኪሮስ ለሕይወትየ በሰዓ ሠርኩ፤ አድኅነኒ ወባልሀኒ በጽንዐ እዴከ ዝኩ፤ ቅድመ ይንሥአኒ ለዓለም መልአኩ፤

ኦ አምላከ አቡነ ኪሮስ ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ..... ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቡነ ዘበሰማያት...

✝ ✝ ✝

17. ለአጻብዒከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለእግር ጥፍሮችህም ኹሉ እና ለጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ አርአያው ለሚያምር ቁመትህም ሰላምታ ይገባል፤ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! ነቢዩ እንዳለው በዚኽ ዓለም ሳለሁ እንደ ወዲያኛው ዓለም እኖር ዘንድ ከላይ ከሰማይ ሁነህ ምሕረትን ለምንልኝ፡፡

18. ለመልክዕከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ደም ግባቱ ለሚደነቅ (ለሚያምር) መልክህ ሰላምታ ይገባል፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ ከሥጋህ በድን ለነፍስህ መለየትም ሰላምታ ይገባል፤ ኃጥኣንን ማማለድ በልብህ የአደረ ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! አንተን ደጉን (ቸሩን) የጠላ ሰው ቢኖር ሕይወቱን ጠልቶ ሞቱን የመረጠ ሰው ነው፡፡

19. ለግንዘተ ሥጋከ፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ከርቤና ሚዓ በሚባሉ ሽቱዎች ለተገነዘው ለሥጋህ አገናነዝ ሰላምታ ይገባል፤ በንጉሥ ክርስቶስ ፈቃድ ለመቃብርህም ሰላምታ ይገባል፤ ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! የዕለተ ምጽአት መለከት በተሰማ ጊዜ እንደ ሰነፎቹ በውጭ ቁሜ እንዳልቀር መብራትህ ዘይቴን ያብራልኝ፡፡

20. ሰላም ለኪሮስ፡- በከንፈሮቹ አምላኩን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሳመ ለጻድቁ ኪሮስ ሰላምታ ይገባል፤ እግዚአብሔርም በደመና ጋረደው (አሳረገው)፤ ነፍሱ ያለጣር ከሥጋው ትለይ ዘንድ ዳዊት የድምፁዋ ቃና ልብን በምትመሰጠው መሰንቆው ‹የጻድቅ ሰው ሞቱ በእግዚአብሔር ፊት ክቡር ነው› ብሎ ዘመረ (አመሰገነ)፡፡

21. አምኀ ሰላም፡- ጻድቁ አቡነ ኪሮስ ሆይ! ለመልክህ ጥቂት የሰላምታ እጅ መንሻን አቀረብሁ፤ ከሕፃንነቴ ጀምሮ አንተን አባት አድርጌሃለሁና ጻድቁ ኪሮስ ሆይ! በሕይወቴ ፍጻሜ ጊዜ የዚኽ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ ሳይነጥቀኝ በጽኑዕ ቃል ኪዳንህ ፈጽመህ አድነኝ አሜን፡፡

አቤቱ የቅዱስ አቡነ ኪሮስ አምላክ ሆይ!! እኔን ባሪያህን..... ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድነኝ ጠብቀኝም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ አባታችን ሆይ!...

✝ ✝ ✝